አሮና - የፈጣሪ ያለህ! ልጁ ይቅር በይኝ! ይህ የእኔ ስህተት ነው ማድረግ አልነበረብኝም፡፡ እናንተን ለመረዳት ምን ማድረግ እችላለሁ. . .

ፊቶ - ታውቃለህ! ትንሽ ዘግይቷል. . .

አሮና - ፊቶ. . .

*******

## ገቢር ሰባት

የጋራ ተስፋ

ገቢሩ ሲጀመር የአኒ ልቅሶና መንሰቅሰቅ ይታያል

ማርያ (በመናደድ)

- እሺ! እሺ!

አኒ - ሌሎቹስ የታሉ?

ማርያ - ሳይወጡ አልቀሩም በዚህ ሰዓት እዚህ ሊኖሩ አይችሉም::

አኒ - (ትነፋረቃለች)

ማርያ - እሺ ንገሪኝ ምን እንደተፈጠረ!

አኒ - (በሃይል ትተነፍሳለች) እሺ! (ትነፋረቃለች) ይመስለኛል እሱ. . . (ትነፋረቃለች) አላውቅም! አዎ አውቃለሁ . . . ምን ላደርግ እንደምችል አላውቅም::

ማርያ - ምን ልታደርጊ እንደምትችይ ለምን አታውቂም?

አኒ - (ትነፋረቃለች) ምንም ላደርግ አልችልም ምንም መልስ ላገኝለት አልቻልኩም መልስ የለኝም (ትነፋረቃለች) ከዚህ በኋላ ምንም አልጠቅምም (ትነፋረቃለች) ከዚህ በኋላ ምንም አልጠቅምም (ታለቅሳለች) ምንም. . . (ትነፋረቃለች) ምንም (ታለቅሳለች)

አኒ - (ታለቅሳለች)

ማርያ - (በኃይል ትተነፍሳለች) አ! አኒ

አኒ - ሌሎችን ብቻ እንደሚገጥማቸው አስብ ነበር (ትነፋረቃለች፣ ታለቅሳለች)

- ማንም ሰው በራሴ ላይ ይመጣል ብሎ አይገምትም (ትነፋረቃለች)

ማርያ - አኒ!

- አኒ! አሁንም በጭንቀት ላይ ነሽ
- ነገር ግን ይህንን ለማለፍ ጥንካሬ አለሽ

- ከጊዜ በኋላም! ታይዋለሽ! በተስፋና በመረጋጋት መኖር የምትችይበትን ጥንካሬም ታገኛለሽ!

አኒ - (ታለቅሳለች) ተስፋ.. መረጋጋት.. (ታለቅሳለች)

- እኔ ከቫይረሱ ጋር እንደምኖር ነግሬሻለሁ:: (ታለቅሳለች) እንዴት ስለ ተስፋና መረጋጋት ልትነግሪኝ ትችያለሽ? (በጣም ታለቅሳለች)
- ታውቂያለሽ HIV Positive ስትሆኚ (ታለቅሻለች) ኅብረተሰቡ ያገልሻል፣ ይተውሻል (ትነፋረቃለች፣ ታለቅሳለች ታለቅሳለች)
- በዚህ ሰዓት ምንም እነደማትፈሪኝ ልትምይ ትችያለሽ ?(ታለቅሳለች)
- ከቤትሽ እንደማታስወጪኝ ትምያለሽ? (ታለቅሳለች) ትምያለሽ?

ማርያ - አኒ! ራስሽን አረጋጊ

- ለምን እንደዚህ ዓይነት ነገር ትናገሪያለሽ?

አኒ - (ታለቅሳለች)

ማርያ - በሕይወትሽ በራስሽ ማዘንሽን የምታቆሚበት ጊዜ ይኖራል:: ምክንያቱምየምታላክኪው ነገር ባለመኖሩ

አኒ - (ታለቅሳለች) በሌላው የማታላክኪው ጉዳይ ይኖራል?

- (ታለቅሳለች) ነገርግን እንደኔ አይደለሽም ምን አይነት ነገር ውስጥ እንዳለሁ አታውቂም
- (ታለቅሳለች) አንቺ ቫይረሱ የለብሽ (ታለቅሳለች፣ ትነፋረቃለች)

ማርያ - አኒ!

አኒ - (ታለቅሳለች! ትነፋረቃለች)

ማርያ - አኒ! በምን ሁኔታ ውስጥ እንደምታልፊ በትክክል አውቃለሁ!

አኒ - (ታለቅሳለች! ትነፋረቃለች)

ማርያ - እኔም አንቺ እንዳለሽበት ዓይነት ሁዔታ ውስጥ ነኝ

አኒ - እኔም እንዳንቺ ነኝ እያልሽኝ ነው ማለት አንቺም . . .

ማርያ - (አኒ ታለቅሳለች)

- አዎ እኔም ከቫይረሱ ጋር እኖራለሁ:: ካወቅሁ አንድ ዓመት ሆኖኛል፡፡
- ቤተሰቦቼም ያውቃሉ

አኒ - (ታለቅሳለች)

አኒ - አንድ ዓመት ሆኖኛል (እየተነፋረቀች)

- አይደረግም! አንኒ ኤች.አይ.ቪ. አለብሽ

ማርያ - አዎ አኒ ልክ እንዳንቺ ለመጀመሪያ ጊዜ የምጠፋ መስሎኝ ነበር

- ነገር ግን ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ነው የተማርኩት . . .

አኒ - (ታብሰለስላለች)

- ማርያ - ከቫይረሱ ጋር እንዴት እንደምኖርና ራሴን እንድንከባከብ ነው

- ዛሬ ሕይወት ከደስታ ጋር በልበ ሙሉነት እየኖርኩ ነው

- ይህ ሕይወት ጥሩ ይመስለኛል

አኒ - የማይታመን ነው! እንዴት ጠንካራ ሆንሽ ?

ማርያ - በእኔ ለመጣብኝ ሁሉ ጠንካራ ነኝ!

አኒ- ልትረጂኝ እፈልጋለሁ

ማርያ-አብረን ጠንክረን መጓዝ እንችላለን

- እንደ እኛ የእኛን ድጋፍ እና እርዳታ የሚፈልጉ ሌሎች ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ! ምክርም ጭምር እሺ!

አኒ - (በኃይል ትተነፍሳለች)

- እሺ (ታለቅሳለች) ትልቅ ነገር ነው

ማርያም - (ትተነፍሳለች! ትስቃለች)

*******